# “ብዝሀ ህይወትን የመጠበቅ አቅማችን ጎልብቷል”

ኢትዮጲያ ካሏት **11** ብሔራዊ ፓርኮች መካከል የኦሞ ብሔራዊ ፓርክ አንዱ ነዉ፡፡ ፓርኩ **515,200** ሄክታር ስፋት ሲኖረዉ **72** አይነት የአጥቢ እንስሳት ዝርያ፣ **325** አይነት የወፍ ዝርያዎችን እና **9** አይነት የአሳ ዝርያዎችን ይዟል፡፡

ምንም እንኳን ፓርኩ በተፈጥሮ ፀጋ የበለፀገ ቢሆንም በርካታ ችግሮች እየተፈራረቁበት ለአደጋ ተጋልጦ ቆይቷል፡፡ በተለያዩ ምክኒያቶች ፓርኩ በዘመናዊ መልኩ ጥበቃ እንዳይደረግለት የበቂ ኤሌትሪክ አቅርቦት ችግር፣ ማህበረሰቡ በአከባቢ ጥበቃ ያለዉ ዉስን ግንዛቤና ተሳትፎ፣ የበጀትና የመሳሪያዎች እጥረት ፓርኩን በበቂ ሁኔታ ለመጠበቅ አዳጋች አድርጎት ቆይቷል፡፡ ይህም በመሆኑ በፓርኩ ዉስጥ ግጦሽ እንዲስፋፋ፣ ሰዎች ለመኖሪያነት እንዲሰፍሩበት እና ለተለያዩ አላማዎች ደን እንዲጨፈጨፍ ምክኒያት ሆኗል፡፡

አክሽን ፎር ዴቨሎፕመንት እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ብዝሀ-ህይወትን ቀጣይነት ባለዉ መልኩ ለመታደግ ያለመ ፕሮጀክት ከምስራቅ አፍሪካ የአከባቢ ጥበቃ ማዕከልና ኔትወርክ (**HoAREC&N**) ጋር በመተባበር በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

በፓርኩ ዉስጥ የታዳሽ ሀይል በመዘርጋት የነበረዉን የኤሌትሪክ እጥረት ከመቅረፍ ባለፈ ባለፉት **36** ወራት ከነዳጅ ወጪ ከ**1** ሚሊዮን **7**መቶ ሺህ ብር በላይ ማስቀረት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለኤሌትሪክ ሀይል ይዉል የነበረዉ ነዳጅ በፀሀይ በሚሰራ ታዳሽ ሀይል በመቀየሩ ወደ አየር ንብረቱ የበካይ ጋሶች መለቀቅ እንዲቀንስ አስችሏል፡፡ በሌላ በኩል ፕሮጀክቱ ጂፒኤስ፣ ካሜራ፣ ዳታ መሰብሰቢያ የመሳሰሉ መሳያዎችን (ስማርት ቴክኖሎጂ) በማቅረብ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ በማድረጉ በፓርኩ ዉስጥ የሚደረጉ ህገወጥ ድርጊቶችን መቆጣጠር አስችሏል፡፡ ጎጂ የፓርክ ወረራ መቀነስም ተችሏል፡፡

ይህም ሲደረግ የነበረዉን ህገወጥ አደን በመቀነሱ እንስሳትን መታደግ ተችሏል፡፡ ከዚህ አልፎም የብዝሀ-ህይወት ጥናትና ቁጥጥር ማድረግ፣ ከአጎራባች ክልሎችና በጉዳዩ ከሚሰሩ አካላት ጋር የአከባቢ ጥበቃ መረጃዎችን በሰዓቱ መለዋወጥ ተችሏል፣ የብዝሀ ህይወት ጥበቃና ልማት እቅዶችንም ለማሳለጥ አስችሏል፡፡



በፓርኩ ለሚሰሩ ሰራተኞች በጂፒኤስ አጠቃቀም፣ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ስለሚደረግ የፓርክ ጥበቃ፣ የመረጃ አሰባሰብና ትንተና ክህሎት ስልጠና በመስጠት የማብቃት ስራ ተሰርቷል፡፡ የፓርኩ ሰራተኞች የብዝሀ-ህይወት ሁነቶችን ለመከታተልና ለመገምገም የሚረዳ ስልጠና ማግኘታቸዉ ከሚመለከታቸዉ ሀገርአቀፍና አለምአቀፍ ተቋማት ጋር የሚኖራቸዉን ትብብር ያቀላጠፈ ሲሆን በፓርኩ ዙሪያ የሚደረጉ ህገወጥ ተግባራትን በቅንጅት ለመከላከል እያገዘ ይገኛል፡፡

በአከባቢ ጥበቃ ስራ **18** አመታትን ያሳለፉት የኦሞ ብሔራዊ ፓርክ ዋና ሀላፊ አቶ ኑሩ ይመር አክሽን ፎር ዴቨሎፕመንት የተገበረዉ የአከባቢ ጥበቃ ስራ ፓርኩ ከተጋረጡበት አደጋዎች እንዲጠበቅ ስለማድረጉና አሰራሩ ላይ ያመጣዉን ለዉጥ እንደሚከተለዉ ገልፀዉታል፡፡ “አሁን የኦሞ ብሔራዊ ፓርክ  የዉጤታማነትና ቀጣይነት ያለዉ የፓርክ ጥበቃና እንክብካቤ ምሳሌ መሆን ችሏል፡፡ በፀሀይ የሚሰራ ታዳሽ የሀይል ምንጭ ጥቅም ላይ መዋሉ ከፍተኛ ወጪን ቀንሶልናል፣ ፓርኩን ከአደጋ ለመከላከል የነበረዉን ብዙ ልፋትና ችግሮች በማቅለሉ ስራዉ በእጅጉ ተቀላጥፏል፣ ብዝሀ-ህይወት ላይ ያለዉ ጫና ቀንሶ የእንክብካቤና ጥበቃዉ ስራ እንዲጨምር አስቻይ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ከሁሉም በላይ ማህበረሰቡን ማዕከል ያደረገ ስራ በቴክኖሎጂ በመታገዝ በመሰራቱ የአከባቢ ጥበቃ ስራዉ አደጋን የመቋቋም አቅምን የሚገነባ እንዲሆን አስችሏል:: በፕሮጀክቱ አማካይነት በፓርኩ የተከናወነዉ የአከባቢ ጥበቃ ስራ ለአከባቢዉ ነዋሪዎች የኑሮ መሰረታቸዉን የሚደግፉበትን የገቢ ምንጭ የሚያገኙበት እድል ፈጥሯል፡፡ በዚህ ረገድ ከተከናወኑ ስራዎች መሀል የዶሮ እርባታ፣ የእሬት ሳሙና ምርት፣ ዘር ማባዛት፣ ታዳሽ ሀይልን በመጠቀም የገቢ ማስገኛ ስራዎችን መስራት የመሳሰሉትን ኢንተርፕራይዞች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህም በማህበረሰቡ ላይ የባለቤትነት መንፈስ በመጨመር ከፓርኩ ጋር ያለዉን መልካም ግንኙነት አጠናክሯል“



አቶ ኑሩ ይመር-የፓርኩ ዋና ሀላፊ

አክሽን ፎር ዴቨሎፕመንት ከዋና ዋና ተግባሮቹ አንዱ የሆነዉን የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ በማከናወኑ ፓርኩ ብዝሀ ህይወትና ማህበረሰቡ ተጣጥመዉ እንዲያድጉና ተጋላጭነታቸዉ እንዲቀንስ የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡